# የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ

# ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL

ኢሰመጉ የቆመው ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ ልዕልናና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ነው፡፡

**EHRCO stands for democracy, the rule of law and the respect of human rights.**

## የብሄረሰቦች ራስን የማስተዳደር ጥያቄ ዘላቂ መፍትሄ ያሻዋል

## 107ኛ ልዩ መግለጫ

የካቲት 20 ቀን 2000 ዓ.ም

### መግቢያ

ኢትዮጵያ የተቀበለችው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 3 እያንዳንዱ ሰው በህይወት የመኖርና የአካል ደህንነቱ የመጠበቅ መብት እንዳለው ያረጋግጣል፡፡ ኢትዮጵያ ፊርማ የተቀበለችው የሲቪልና የፓለቲከ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳንም በአንቀጽ 6(1) እና 9(1) ላይ ይህንኑ መብት በማረጋገጥ መንግስታት በቃልኪዳኑ የተረጋገጡትን መብቶች በግዛ ቸው የማክበርና የማስከበር ግዴታ እንዳለባቸው በአንቀጽ 2(1)(2) ይደነግጋል፡፡ የኢፌዲሪ ህገ መንግስትም በአንቀጽ 14 ላይ «ማንኛውም ሰው ሰብአዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በህይወት የመኖር የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው» ሲል ያረጋግጣል፡፡

በአገራችን እነዚህ መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶች በተለያዩ ምክንያቶች እየተጣሱ ይገኛሉ፡፡ ራስን ከማስተዳደር ጥያቄ ጋር ተያይዘው በሚፈጠሩ ግጭቶች ሳቢያም ከፍተኛ የመብቶች ጥሰት እየደረሰ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ(ኢሰመጉ) በዚህ 107ኛ ልዩ መግለጫው በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በደራሼ እና ኮንሶ ልዩ ወረዳዎች የተለያዩ ቀ/ገ/ማህበራት በሚኖሩ የገዋዳ (አሌ) ብሄረሰብ አባላትና በመንግስት ሀይሎች (የፌዴራል ፖሊስና የመከላከያ ሰራዊትን ጨምሮ) መካከል በተፈጠረ ግጭት የደረሰውን የሰብአዊ መብቶች ጥሰት በቦታው በመገኘት አጣርቶ እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡

### ዝርዝር

የገዋዳ (አሌ) ብሄረሰብ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ከሚኖሩት በርካታ ብሄረሰቦች አንዱ ነው፡፡ የብሄረሰቡ አባላት ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ በደራሼ ልዩ ወረዳ በሚገኙ 10 ቀ/ገ/ማህበራት፣ በኮንሶ ልዩ ወረዳ በሚገኙ 7 ቀ/ገ/ማህበራት እና በደቡብ ኦሞ በሚገኙ 10 ቀ/ገ/ማህበራት ውስጥ ይኖራሉ፡፡ ራሳችንን ችለን በልዩ ወረዳ መደራጀት ሲገባን በተለያዩ ወረዳዎች መካለላችን ብሄረሰቡ ስሙን እንዲያጣ፣ ባህልና ቋንቋውን እንዳያሳድግ በአጠቃላይ ራሱን ከማስተዳደር ተጠቃሚ እንዳይሆን አድርጎታል በሚል የብሄረሰቡ ተወካዮች ጥያቄያቸውን ለሚመለከታቸው የክልልና የፌዴራል አካላት ሲያመለክቱ ቆይተዋል፡፡

ይሁን እንጂ ይህ በልዩ ወረዳ እንካለል የሚል ጥያቄያቸው አሁንም ድረስ አጥጋቢ ምላሽ እንዳላገኘ የብሄረሰቡ ተወካዮች ይናገራሉ:: በአንጻሩ ለምን እንዲህ አይነት ጥያቄ ታነሳላችሁ በሚል የብሄረሰቡ አባላት ለእስራት፣ ከስራ መባረርና ለሌሎች የበቀል እርምጃዎች ሰለባ ሆነዋል ሲሉ የብሄረሰቡ አባላት አመልክተዋል::

ጥያቄያቸው ተገቢውን መፍትሔ ባለማግኘቱ ሁኔታው እየተካረረ መጥቶ ጥር 24 ቀን 2000 ዓ.ም ሌሊት አስር የሚደርሱ የፌዴራል ፖሊስ አባላት ከብሄረሰቡ ወኪሎች አንዱ ከሆኑት አቶ ሮባ አበበ ቤት ገብተው አቶ ሮባን ሲያጧቸዉ ልጆቻቸውን ፍሬው ሮባና ውባለም ሮባን ከእንቅልፋቸው ቀስቅሰው አባታችሁን አምጡ እያሉ ድብደባ እንደፈጸሙባቸው ተጎጅዎች ገልጸዋል:: ከዚህም በተጨማሪ አባታችሁን ካላመጣችሁ በማለት በመኪና ሊወስዷቸው ሲሉ የአካባቢው ህዝብ ወጥቶ በመቃወሙ ለቀናት የዘለቀ ከፍተኛ ግጭት ተቀስቅሶ ለበርካታ ሰዎች መገደልና መቁሰል ምክንያት ሆኗል::

ኢሰመጉ የደረሰውን የመብቶች ጥሰት ለማጣራት ወደቦታው የተንቀሳቀሰ ቢሆንም ይህ መግለጫ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ውጥረቱ ያልበረደ በመሆኑ በግጭቱ ምክንያት ጉዳት በደረሰባቸው ቦታዎች ሁሉ በመገኘት የደረሰውን ጥፋት በሙሉ ለማጣራት አልቻለም:: ስማቸው በሚከተሉት ሰንጠረዦች የተመለከተው ግለሰቦች መገደላቸውንና መቁሰላቸውን ከተጎጅዎች ቤተሰቦች ምስክርነት፣ ከአካባቢው የመንግስት ሀላፊዎች ቃልና ከሌሎች ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ችሏል::

**ሰንጠረዥ1- በግጭቱ የተገደሉ**

| ተ.ቁ | ስም | ዕድሜ | ስራ | አድራሻ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ዘነበ ማሞ | 54 | አርሶ አደር | ላሊቾ ቀ/ገ/ማ |
| 2 | ኢታኩ አሹ | 35 | ,, | ,, |
| 3 | አመቱ አንኬ | 47 | ,, | ,, |
| 4 | ጎድዬ ገዛኸኝ | 32 | ,, | ,, |
| 5 | ተገኝ ቶያ | 20 | ,, | ,, |
| 6 | ኦጆሱ ኦንጎ | 18 | ,, | ,, |
| 7 | ጅባታ ካናምባ | 40 | ,, | ,, |
| 8 | ኩዳ እተነነ | 40 | ,, | ,, |
| 9 | ሱካማ ሲሳይ | 35 | ,, | , |
| 10 | ክትልሚ ክሞ | 55 | ,, | ኦልተሜ ቀ/ገ/ማ |
| 11 | ካላ ሞዳሴ | 33 | ,, | ላሊቾ ቀ/ገ/ማ |
| 12 | እተነኤ ኦልተሻ | 62 | ,, | ,, |
| 13 | ኩሾ ጥኖ | 40 | ,, | ወርዛ ቀ/ገ/ማ |
| 14 | ዋርሌ ዋንሶ | 38 | ,, | ገዋዳ ቀ/ገ/ማ |
| 15 | ማላ ማታማ | 25 | ,, | ,, |
| 16 | ዘውዱ ዋዎ | 26 | ,, | ,, |
| 17 | ወገኔ ጸጋዬ | 14 | ,, | ቱሩባ ቀ/ገ/ማ |
| 18 | አጉሌ አየለ | 30 | ,, | ,, |
| 19 | ጋርታ መንገሻ | 38 | ,, | ,, |
| 20 | ዱባለ ኩአኔ | 38 | ,, | ላሊቾ ቀ/ገ/ማ |
| 21 | ሺላ ኩርጣ | 42 | ,, | ,, |
| 22 | ታከቴ ቀሳ | 42 | ,, | ,, |
| 23 | ጥላሁን ጥኑ | 20 | ,, | ገርገማ ቀ/ገ/ማ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 24 | አስፋው ወ/ኪዳን | 36 | የደራሼ ወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤት ሰራተኛ | ጊዶሌ |
| 25 | ኮንስታብል አሸናፊ ገዘሙ | 32 | የደራሼ ወረዳ ፖሊስ ባልደረባ | ” |
| 26 | ኮንስታብል ገነቱ አባቱ | 33 | ” | ” |
| 27 | ኮንስታብል መስፍን አየለ | 35 | ” | |
| 28 | ም/ሳጅን ወንድሙ ሀዳ | | ” | |
| 29 | ኦፒቶ ኦማ | | የፌዴራል ፖሊስ ባልደረባ | ጋምቤላ |
| 30 | ተስፋ ማሩ | | ” | ጎጃም |
| 31 | አዲሱ | | ” | |
| 32 | አብርሀም | | ” | ትግራይ |
| 33 | ኮ/ል ባልዴ | | ” | |

## ሰንጠረዥ 2-በግጭቱ የቆሰሉ

| ተ.ቁ | ስም | ዕድሜ | አድራሻ | ዝርዝር ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ታደሰ አማኑ ኩሴ | 27 | ሳሊቾ | ከፌዴራል ፖሊስ ጋር በተደረገ ግጭት በጥይት ተመትቶ የቆሰለ |
| 3 | ሮባ ኡንቼቾ | 28 | ” | ” |
| 4 | አእምሮ ሳህለ | 29 | ወላንጎ | ” |
| 5 | ማቹሌ ማማቶ | 17 | ” | ” |
| 6 | አወቁ አዲንጌ | 16 | ” | ” |
| 7 | ቺቾ እንጬ ግራቶ | 13 | ወርዛ | ” |
| 8 | ጋኖሌ ጋኞ | 20 | ጉማ | ” |
| 9 | እጅጉ ቲቶ | 25 | ” | ” |
| 10 | አግሶ ማንጎ | 35 | ወርዛ | ” |
| 11 | ኩሴ ናአቶ | 38 | ” | ” |
| 12 | ጭራ ሽታኔ | 40 | ሎክቴ | ” |
| 13 | ተቱቤ ጉላሴ | 30 | ሳሊቾ | ” |
| 14 | ጉሻቶ ጎልቲቶ | 28 | ድክንቲ | ” |
| 15 | ከሸንቃቤ አሮኤ | 30 | ” | ” |
| 16 | ታደሰ አማኑ | 30 | ሳሊቾ | ” |
| 17 | እመሴ እባይሳ | 35 | ” | ” |
| 18 | ዘውዱ አንዳልቶ | 15 | ” | ” |
| 19 | ሹቃቶ ትኮካ | 47 | ” | ” |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 20 | ደበላ ካዕኔ | 43 | ” | ” |
| 21 | ታምራት ገዛኸኝ | 41 | ” | ” |
| 22 | አዲሱ ያገና | 52 | ” | ” |
| 23 | መጋባ ችቻኤ | 70 | ” | ” |
| 24 | ደገፉ አካሶ | 71 | ” | ” |
| 25 | ፈዶ አርሶ | 25 | ” | ” |
| 26 | ጋናማ ጋቴ | 25 | ጉማ | ” |
| 27 | ጀርቡ ጉርሼ | 35 | ” | ” |
| 28 | አንቡቴ ከርተውሌ | 40 | ገዋዳ | ” |
| 29 | ማርታ ማሳቶ | 12 | ” | ” |
| 30 | ጉያና ጉዶሶ | 17 | ” | ” |
| 31 | ናኢቶ አሻገሬ | 41 | ቱርባ | ” |
| 32 | ኩሴ ከርሳ | 18 | ገዋዳ | ” |
| 33 | ሳንዱ ገርሳ | 40 | ገርጋማ | ” |
| 34 | ጉይና ሳቴ ጎርጃ | 16 | ” | ” |
| 35 | እሽቱ ወንድሙ | 55 | ወላንጎ | ” |
| 36 | ጉርዳታ ኩሴ | 26 | ገዋዳ | ” |
| 37 | ኢግዛ ሀመ | 40 | ” | ” |
| 38 | ሳጅን አቡበከር አብዱልጀሊል | 35 | አሶሳ | የፌዴራል ፖሊስ ባልደረባ |
| 39 | ሰሙ አበበ | | ደራሼ | የወረዳው ፖሊስ ባልደረባ |
| 40 | ሙለታ ዲሳሳ | | ኮንሶ | ” |
| 41 | ጥላሁን ደነቀ | | | ” |
| 42 | ሳጅን አለሙ መንገሻ | | | የፌዴራል ፖሊስ ባልደረባ |
| 43 | ኮንስታብል ሁሴን | | | |
| 44 | ኮንስታብል የማነ | | | |
| 45 | ኮንስታብል ሽፈራው | | | |
| 46 | ኮንስታብል አፋዱ | | | |
| 47 | ጋሳሳ ጋርሳ | 18 | ገዋዳ | አርሶ አደር |
| 48 | ኩያኖ ኮይሳ | 14 | ” | ተማሪ |
| 49 | ናኦቶ አሽብሬ | 40 | ወላንጎ | አርሶ አደር |
| 50 | አንብቴ ጋርታውሌ | 55 | ገዋዳ | ” |

## ማጠቃለያ

- አሁንም በአካባቢው ውጥረት እንደነገሰ ይገኛል:: በመሆኑም ይህ መግለጫ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ አካባቢው በመከላከያ ሰራዊት እየተጠበቀ ሲሆን ግጭቱም ሙሉ በሙሉ አልበረደም:: በዚህም የተነሳ የደረሰውን የሰብአዊ መብቶች ጥሰት መጠን ሙሉ በሙሉ ለማወቅ አልተቻለም::

- ኢሰመጉ የገዋዳ (አሌ) ብሄረሰብ አባላት ያነሱት ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ በህገመንግስቱ አግባብ ሊፈታ ሲገባው እየተጓተተ መጥቶ እንዲህ አይነት የከፋ ጥፋት በማስከተሉ የተሰማውን ሀዘን እየገለጸ የደረሰው ጥፋት በገለልተኛ አጣሪ ቡድን እንዲጣራና ለደረሰው የህይወት ጥፋት፣ የአካል ጉዳትና የንብረት ውድመት ተጠያቂ የሆኑት ግለሰቦች ለፍርድ እንዲቀርቡ ይጠይቃል።

- መንግስት የዜጎችን የህይወት፣ የአካል ደህንነትና የንብረት መብቶችና ነጻነቶች በማስጠበቅ በኩል ያለበትን ህገመንግስታዊ ግዴታ በአግባቡ እንዲወጣ፤

- በግጭቱ ለተገደሉ ግለሰቦች ቤተሰቦች፣ እንዲሁም ለቆሰሉና ንብረታቸው ለወደመባቸው ሁሉ ተመጣጣኝ ካሳ እንዲከፈላቸው፤

- በመጨረሻም ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተው ግጭቱ የተከሰተው የብሄረሰቡ ጥያቄ ዘላቂ ህጋዊ መፍትሄ ባለማግኘቱ ነውና የሚመለከተው የመንግስት አካል የተነሳውን ራስን የማስተዳደር ጥያቄ ከህገመንግስቱ አንጻር አጥንቶ ዘላቂ እልባት እንዲፈልግለት፤ ዛሬም ኢሰመጉ ይጠይቃል

በተጨማሪም ለሰብአዊ መብቶች መከበርና ለሕግ ልዕልና የቆማችሁ ዜጎች፣ ብሔራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የመንግሥታትና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች የኢትዮጵያ መንግስት ለደረሰው የህይወት ጥፋት፣ የአካል ጉዳትና የንብረት ውድመት ተጠያቂ የሆኑትን ግለሰቦች ለፍርድ እንዲያቀርብና ለዜጎች የህይወት፣ የአካል ደህንነት የንብረት መብቶችና ነጻነቶች በቂ ጥበቃ እንዲያደርግ እንደዚሁም የሚነሱ የቡድን መብት ጥያቄዎች በህግ አግባብ ብቻ እንዲፈቱ ለማስቻል የሚጠበቅበትን ሁሉ እንዲያደርግ የበኩላችሁን ግፊት ታደርጉ ዘንድ ኢሰመጉ ይጠይቃል።

ግልባጭ

- **ክቡር አምባሳደር ተሾመ ቶጋ**
  የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አፈጉባኤ
  ፖ.ሣ.ቁጥር 80001፣ ፋክስ (251-11) 155 0900
  ስልክ (251-1) 1241013
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ክቡር አቶ ደግፌ ቡላ**
  የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈ ጉባኤ
  ፖ.ሣ.ቁጥር 80001፣ ፋክስ (251-11) 155 0722
  ስልክ (251-11) 124 2301
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ክቡር አቶ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ**
  የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕሬዚዳንት
  ፖ.ሣ.ቁጥር 1031፣ ፋክስ (251-11) 155 2020
  ስልክ (251-11) 551 8850
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ**
  የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር
  ፖ.ሣ.ቁጥር 1031፣ ፋክስ (251-11) 155 2020

ስልክ (251-11) 122 6767
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- **ክቡር አቶ ሲራጅ ፈጌሣ**
  የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር
  ፖ.ሣ.ቁጥር 1370፣ ፋክስ (251-11) 552 0000
  ስልክ (251-11) 552 0000
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ክቡር አቶ አሰፋ ከሲቶ**
  የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትሕ ሚኒስትር
  ፖ.ሣ.ቁጥር 1370፣ ፋክስ (251-11) 552 0874
  ስልክ (251-1) 551 5099
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ክቡር አቶ ፍቅሩ ኛካል**
  የደቡብ ብሔር፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ
  ፖ.ሣ.ቁጥር 18፣ ፋክስ (251-46) 220 1950
  አዋሳ፣ ኢትዮጵያ
- **ክቡር አምባሳደር ካሣ ገ/ሕይወት**
  የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር
  ፖ.ሣ.ቁጥር 1165፣ ፋክስ (251-11) 645 9290
  ስልክ (251-1) 645 9228
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ክቡር አቶ አባይ ተክሌ**
  የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ዋና እምባ ጠባቂ
  ፖ.ሣ.ቁጥር 2459፣ ፋክስ (251-11) 645 9229
  ስልክ (251-11) 663 5090፣ 663 5363
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ